# ኢትዮጵያና የዲያስፖራ ዕጣ ፈንታ

መለስ ዓ.

የዓለም አቀፍ ዋና ዋና ተቋማት፣ የባለብዙ ወገን ኮርፖሬሽኖችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከዲያስፖራው የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ (Remittances) ለአገሮች የኢኮኖሚ ልማት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው ይስማማሉ:: በየዓመቱ 200 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ለስደት የሚዳረጉ እንደሆነ የተለያዩ ሰነዶች ያመለክታሉ:: የእነዚሁ ስደተኞች አብዛኛው መዳረሻም አሜሪካና አውሮፓ እንደሆኑ ይነገራል::ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የመካከለኛው ምስራቅና የሩቅ ምስራቅ አገሮች ተመሳሳይ መዳረሻዎች ሆነዋል:: ፒተር ኤ-ጄፍሬይ የተባሉ በዳያስፖራ ላይ በርካታ ፅሁፎችን የሚያቀርብ ጋናዊ አምደኛ እንደገለፁት የአብዛኛው ዲያስፖራ ምንጮች ደቡብ አሜሪካ፣ አፍሪካና ኤሲያ እንደሆኑ በመጥቀስ የብሪተንውድስ ተቋማት (የዓለም ባንክና የዓለም ገንዘብ ድርጅት) ከሚሰጡት የልማት እርዳታ ይልቅ በውጭ ከሚገኙ ዲያስፖራዎች የሚላከው ገንዘብ የበለጠ ነው:: የኢትዮጵያ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ዳይሬክተር ዶክተር ወልዳይ አምሃ በበኩላቸው በቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትና ከውጭ የሚላከው ገንዘብ መካከል ያለው ልዩነት ተቀራራቢ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር ከተሰደዱ ዜጎች የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል:: ለምሳሌ ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች ውስጥ ጋና ውጪ ከሚገኙ ዜጎቿ ከፍተኛውን ገንዘብ በማግኘት ተጠቃሽ ናት:: ለጋና ከዲያስፖራ የሚገኘው ገንዘብ በሶስተኛ ደረጃ የሚገኝ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ነው:: አገራችን ባለፉት አስር ወራት 780 ሚሊዮን ዶላር በህጋዊ የባንክ ሃዋላ ልውውጥ እንዳገኘች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገልፆ ይህም በዕቅድ ከተያዘው 9 በመቶ በላይ እንደሆነ ይፋ ያድርግ እንጂ ግብፅና ኬንያን ከመሳሰሉ የአካባቢያችን አገሮች ጋር እንኳን የሚወዳደር አይደለም::

ዲያስፖራን ከውጭ ከሚገኝ ገንዘብ ጋር ማዛመድ የተለመደ ይሁን እንጂ በእውቀትና ክህሎት ሽግግር ላይ ጉልህ ሚና አላቸው:: ቻይና በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢኮኖሚው መስክ ተዓምራዊ ለውጥ (Economic Miracle) እንድታሳይ ህንድም አገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ እንድትሰለፍ የመካከለኛ የህብረተሰብ ክፍል ለመገንባት ጉልህ ስፍራ ነበራቸው:: በፖለቲካውም መስክ ዳያስፖራው በሚኖሩበት አገር የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ተፅዕኖ የማሳደር ብቃት እና አቅም እንዳላቸው የሚታወቅ ሲሆን ለዚህም አይሁዶች በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ መጥቀስ ይቻላል:: ጆን

ሜርሻምር እና ስቴፈን ዎልት የተባሉ የቺካጎና ሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች "The Israel Lobby" በተሰኘ መፅሃፋቸው አሜሪካ በአይሁዶችና አፍቃሪ አይሁድ በሆኑ ግለሰቦችና ተቋማት ተፅዕኖ ሳብያ እስራኤልን በተመለከተ ስትራቴጂያዊ እና አንዳንዴም ከሞራል አንፃር ጠቃሚ ያልሆነ ፖሊሲ ታራምዳለች ሲሉ ገልፀዋል:: እነዚህን የዲያስፖራ ተፅዕኖ የተረዱ ወገኖች በሌላ አገር ያሉ ዜጎቻቸውን ለመጠቀም የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም::

## <u>እያነቡ እስክስታ</u>

የኢትዮጵያውያን የውጭ አገር ስደት ከአርባ ዓመት በላይ ዕድሜ እንደሌለው ይነገራል:: በተለያዩ ምክንያቶች ውጭ አገር ሄዶ መቅረት ነውር ነበር:: ዶ/ር ወልዳይ አምሃ እንዳመለከቱት ለኢትዮጵያውያን ስደት ዋነኛ ምክንያቶች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ናቸው:: የኢትዮጵያ ዲያስፖራዎች ቁጥር በትክክል ባይታወቅም አንድ ሚሊዮን ያህል እንደሚሆኑ ይነገራል:: ሮበርት ኮሆን የተባሉ ሶሺዮሎጂስት ዜጎች በተለያዩ ግፊቶች(push/pull factors) ሳቢያ ለስደት እንደሚዳረጉ ይገልፃሉ:: ተመራማሪው ሰዎች የጥቃት ሰለባ በመሆናቸው፣ ለጉልበት ሥራ፣ ለንግድ ወረራ እና የባህል ወረራ ለማድረግ ሊሰደዱ ይችላሉ:: ይህንንም በምሳሌ ሲያስረዱ አይሁዶች በመጠቃታቸው፣ ህንዶች ለሥራ፣ ቻይናዎችና ሊባኖሶች ለንግድ፣ አይሪሾች እንዲሁም ሩሲያዎች ለወረራ ስፔኖች ደግሞ ለባህል ጉዳይ አሜሪካ እንደገቡ ጠቅሰዋል:: በተጨማሪም ማህበረሰቦቹ ከእነዚሁ አንዱና ከዚያም በላይ ቅርፅ ሊይዙ ይችላሉ::

ዶ/ር አብይ ጣሴ የተባሉ የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራ ከአገራቸው የወጡበትን ጊዜ በአራት ምዕራፍ ከፋፍለውታል:: ተመራማሪው የመጀመሪው የሚሉት ከ1966 ዓ.ም. በፊት ያለውን ጊዜ ነው:: በርካታ የአፍሪካ አገሮች ዜጎች ነፃነታቸውን ሲያገኙ ወደቀድሞ ቀኝ ገዢዎቻቸው በመሄድ ይኑሩ እንጂ ኢትዮጵያ በጣሊያን የወረራ ወቅት ለአምስት ዓመታት ብትቆይም አገራቸውን ጥለው ወደ ጣሊያን የተሰደዱት 2,345 ብቻ ነበሩ:: አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች ደግም ከንጉሳዊ ስርዓት ጋር ቁርኝት ያላቸውና ለትምህርት የሄዱ ኢትዮጵያውያን ናቸው::

ሁለተኛው ምዕራፍ ከ1966-1974 ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲሆን በዚህ ወቅት በርካታ ኢትዮጵያውያን መጀመሪያ ወደ ጎረቤት አገሮች በመጥፋት በአሜሪካና አውሮፓ ለመኖር

የተገደዱ ናቸው።አብዛኛው ዲያስፖራ ኢትዮጵያዊ ወደ አሜሪካ እና አውሮፓ የተሰደደው ወታደራዊ ደርግ ስልጣን ሲይዝ ሲሆን ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሄዱት ደግሞ ከሥራ ጋር በተያያዘ ነው። በሞንታና ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ፒተር ኮሆን ዋሽንግተን ውስጥ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ ባደረጉት ጥናት ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ከአገር የተሰደዱት በፖለቲካ ምክንያት እንደሆነ መገንዘባቸውን ይገልፃሉ። በሶስተኛ ደረጃ ከ1974-84 ዓ.ም የተቀመጡት ደግሞ ቀደም ሲል የተሰደዱ ቤተሰቦቻቸውን ለመቀላቀል እንዲሁም በቱሪስት ቪዛ ወደ አውሮፓና አሜሪካ በመሄድ እዚያው የቀሩ ናቸው። አራተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የመንቀሳቀስ መብት በመከበሩ የተሰደዱ ምሁራንና በተለያዩ ግጭቶች ሳቢያ አገራቸውን ጥለው የወጡ ናቸው እንደ ዶ/ር አብይ አስተያየት።

እነዚሁ ኢትዮጵያውያን በተለይም የተሻለ ትምህርትና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘታቸው እንዳለ ሆኖ አገራቸውን በተመለከተ በሚቻላቸው ሁሉ አለንልሽ ማለታቸው ባይቀርም አገሪቱ ከዲያስፖራ የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። እ.ኤ.አ. 2001 18 ሚሊዮን፣ 2005 ደግሞ 174 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነበር። ዘንድሮ የተገኘው ከእዚህ ጋር በ300 ፐርሰንት የበለጠ ነው። ይህ በንፅፅር ከመንግሥት አልባ ሶማሊያ ጋር እንኳ የሚወዳደር አይደለም። ኢትጵያውያን ከውጭ ምንዛሪ በተጨማሪ ወደ አገራቸው በመምጣት ክህሎቶቻቸውንና ልምዶቻቸውን በማካፈል የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚፈጥሩበት ዕድል እስከ ቅርብ ጊዜ አልነበረም። ዓለማቀፉ የስደተኞች ድርጅት (አይ.ኦ.ኤም) ዳያስፖራው ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ከሚሰሩ አገሮች ኢትዮጵያ አንዷ እንደሆነች እማኝነቱን ገልዋል። የኢትዮጵያ መንግስት ዲያስፖራው በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት መስክ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ የአገሪቱን ገፅታ በመገንባት ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዲኖራቸውና በውጭ አገር መብታቸው እና ጥቅማቸው እንዲከበር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥር በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ጉዳይ የሚከታተል ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ማቋቋሙ ይታወሳል ። በክልሎች ደረጃም የዳያስፖራውን ጉዳይ የሚከታተል አካል መኖሩ መንግስት የሰጠውን ልዩ ትኩረት ያሳያል። ደህና ሆኖ የሚቀሩ ሥራዎች እንዳሉ ይታያል። ዲያስፖራውም ቢሆን በእንባ እየታጠበና ወደ ኋላ እያየ ትቷት በሄዱባት አገሩ ጉዳይ ተመልካች ብቻ አይደለም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ ወቅቶች ወደ አገሩ በመመለስ በተወሰነ መልኩ የልማቱ ትሩፍት ምንጭም ተቋዳሽም ሆኗል።

## ዳያስፖራ ወይስ ዳያስፖራ

ዳያስፖራ የአንደኛውን የዓለም ጦርነት ተከትሎ የተለመደ ቃል ይሁን እንጂ የተለያዩ ማህበራዊ ሳይንስ መስኮች የተለያየ ትርጉም ይሰጡታል። የቃሉ መነሻ ከግሪክ ሲሆን ጥሬ ትርጉሙም የዘር መበተን (scatering of seeds) ማለት ነው። ቃሉ አንድ ህዝብ ወይም ማህበረሰብ ከተወሰነ አካባቢ በኃይል ከመባረር ጋር የተያያዘ ሲሆን አይሁዶች የዚህ ጥንታዊ ምሳሌዎች ናቸው። የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ዳያስፖራ ሶሺዮሎጂካል ክስተት ነው ሲሉ ይገልፁታል። ፕሮፌሰር ሮበን ኮሆን የዳያስፖራ ንቅናቄ ምክንያት የተለያየ ብቻ ሳይሆን ፅንሰ ሃሳቡም ሆነ ትርጉሙ በየጊዜው ይለዋወጣል ሲሉ ይከራከራሉ። ዶ/ር ዊሊያም ጄ-ኮህንም ትርጉሙ ሰፊ እንደሆነ በመጥቀስ ለሶሺዮሎጂስቶችና አንትሮፖሎጂስቶች ከትውልድ ቦታቸው ጋር የተወሰነ ግንኙነት አልያም የሥነ-ልቦና ቁርኝነት ያላቸው ማህበረሰቦችን መሰደድ ያካትታል ቢሉም ይህ ትንተና ከሚኖሩበት አገር ቢሰደዱም በባህል ተዋህደው እንደተወለዱበት አገር የሚኖሩ ዜጎችን ለምሳሌ አፍሪካ አሜሪካውያንን ላያቅፍ ይችላል። ከቀዝቃዛው የአለም ጦርነት በኋላ ይበልጥ እየተሰራበት ያለው ይህ የህብረተሰብ ክፍል ከኢንተርኔት መስፋፋት በኋላ ይበልጥ እየተጠናከረ መምጣቱን በተለያዩ የዓለምአቀፍ መድረኮች ከአፍሪካ ህብረት እስከ ቡድን ስምንት አገሮች ድረስ አጀንዳ መሆኑ ስለዳያስፖራው ያለው ፋይዳ ግንዛቤ ያገኘ መሆኑን አመላካች ነው።

በልማዳዊ አስተሳሰብ ዳያስፖራን ከገንዘብ ምንጭነት በዘለለ ማስቀመጥ የተለመደ ቢሆንም የጤና፣ የትምህርት፣ የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር እጥረቶችን ለመቅረፍ ጉልህ ሚና አላቸው። ፓርቺ ሚሽራ "የተማሩ ሰዎች ፍልሰት" በሚል ርዕስ በፃፉት መፅሃፍ እንደገለፁት ዳያስፖራ የንግድ፣ ቱሪዝም፣ ኢንቨስትመንት መረቦችን በመዘርጋት ለአገራቸው አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ዳያስፖራው የትውልድ አገራቸውንና የሚኖሩበትን አገር ፖሊሲ፣ ባህልና ስነ-ልቦና ጠንቅቀው ስለሚያውቁ በሽርክና ለመስራት እንዲሁም የአገራቸውን የልማት መልዕክትን በተቀረፀበት መልክ ለማስተላለፍ የሚያስችል ልዩ ባህርይ አላቸው። ጄኒፈር ብረንከር የግሎባላይዜሽን ጥናት ማዕከል በሚያወጣው ህትመት ይህን ባህሪይ ድቅል ባህል (culturally hybrid) ሲሉ ይገልፁታል። በዚህ ባህሪያቸው የተነሳም በሚኖሩበት አገር ያለውን ልምድ በመቀመር ለአገራቸው ውሳኔ

ሰጪ አካላት ምክር ይሰግሳሉ፡፡ የዳያስፖራ ማህበረሰብ የትውልድ አገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅምን ለማስከበር የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ ፅሁፌ መግቢያ ላይ የጠቀስኳቸው የቺካጎና ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች በዝርዝር እንደሚያስረዱት አይሁዶችና አፍቃሪ አይሁዶች የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች አሜሪካ በመካከለኛው ምስራቅ ብቻ ሳይሆን ስትራቴጂካዊ ወዳጆች ናቸው በምትላቸው የአውሮፓ አገሮች ሳይቀር የእስራኤልን ጥቅም የሚጎዳ ፖሊሲ እንዳታራምድ ጠንካራ ተፅእኖ ያደርጋሉ፡፡ ተመራማሪዎቹ እንደሚሉት ጆርጅ ቡሽ የሳዳም ሁሴን አስተዳደር ላይ ጦርነት እንዲያውጁ ለማድረግ እነዚህ ወገኖች የተሳካ ተግባር አከናውነዋል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ የሚኖሩባቸው አገሮች መሣሪያ በመሆን አገራቸውን በሚጎዱ ተግባራት ላይ እንደሚሰማሩ ግልፅ ነው፡፡

## <u>ቪቫ ዳያስፖራ</u>

መንግስት ለኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመስጠቱ በአገራቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች ውስጥ ያላቸው አስተዋጽኦ እየተጠናከረ መጥቷል፡፡ ዳያስፖራው ከቀረጥ ነፃ መብት፣ በውጭ ምንዛሪ ገንዘቡን ባንክ እንዲያስቀምጥ ዕድል ፈጥሮለታል፡፡ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚሰጣቸው ቢጫ የመታወቂያ ካርድ እንደ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በኢንቨስትመንት ላይ መሰማራት ችለዋል፡፡ ዳያስፖራው በአሁኑ ወቅት በሪልስቴት፣ በፋብሪካ፣ በሆቴል እና ኮሚኒኬሽን ዘርፎች ጉልህ ተሳትፎ አለው፡፡ በያዝነው ዓመት ብቻ 107 የሚሆኑና 400 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ ፕሮጀክቶች በዳያስፖራ ቀርበዋል፡፡ ሥራቸው ሲጠናቀቅ ለባለሃብቶቹም ሆነ ለኢትዮጵያውን ወገኖቻቸው የሚፈጥረውን የሥራ ዕድል መገመት ይቻላል፡፡ ዳያስፖራው በውጭ ምንዛሪ ግኝት እንዲሁም ኢንቨስትመንት ላይ ካለው አስተዋፅኦ በተጨማሪ አገሩን በዕውቀቱ ያገለግላል፡፡ በዚህ ረገድ በግንባር ቀደም የሚጠቀሰው የሰሜን አሜሪካ የጤና ባለሙያዎች ማህበር ነው፡፡ ማህበሩ በየዓመቱ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ለእናት አገሩ ድጋፍ በማድረግ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት 23 የጤና ባለሙያዎች በተለያዩ ሆስፒታሎች አገራቸውን በማገልገል ላይ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 52 ባለሙያዎች በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለማገልገል ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

እነዚህ አዎንታዊ እርምጃዎች ይሁኑ እንጂ ኢትዮጵያዊ ዳያስፖራ ካለው ቁጥር ጋር የሚመጣጠን አይደለም፡፡ ከዚህ የባሰው ግን ዕድቁ ቀርቶ እንዲሉ አገሬ ከሚለው

መፈክር ውጪ ለአገራቸው ምንም ፋይዳ ያለው ተግባር የማያከናውኑ ፅንፈኛ እና ጫጫ ዳያስፖራ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ዳያስፖራዎች አብዛኛውን ግን ዝምተኛውን ዳያስፖራ (Silent Majority) ውጠውታል፡፡ እኔ እነዚህን ዳያስፖራዎች በሁለት ነው የምከፍላቸው፡፡ አንዳንዶቹ ስለአሁኒቷ ኢትዮጵያ በቂ እውቀት የላቸውም፡፡ አልተማሩም ወይንም ጥሪት አላፈሩም፡፡ ከዛሬ 20 እና 30 ዓመታት በፊት ከአገር የወጡ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ዛሬም "የጠቅል አሽከር" ቢሉ ሊፈረድባቸው አይገባም፡፡ ሌሎች ደግሞ በጭፍን የጥላቻ ፖለቲካ ደንብሸው ከሰማይ መና እንኳ ቢወርድ ይህ መንግስት እስካለ ድረስ እውቅና መስጠት አይፈልጉም፡፡ በአገራችን የመቻቻል ፖለቲካ እንዲኖር የሚሹም አይመስሉም፡፡ ዊሊያም ሳፍራን የተባሉ ሶሺዮሎጂስት ዳያስፖራ አንድ ወጥ የሆነ መልክ ወይም ባህርይ የለውም ይላሉ፡፡ እኔም እስከምረዳው ድረስ ዳያስፖራው አንድ አይነት እንዲሆን አልጠብቅም፡፡ ይሁን እንጂ ዲሞክራሲ በሰፈነበት ዓለም ውስጥ እኖራለሁ አልያም ለዲሞክራሲ እታገላለሁ የሚል ዳያስፖራ እንዴት ዲሞክራሲያዊ ባህሪ የለውም፡፡ ሪፖርተር ጋዜጣ በአንድ ወቅት በርዕሰ አንቀጹ አንዳንድ ዳያስፖራዎችን ውሃ ውስጥ እየኖረ ከማይረጥበው ዓሣ ጋር ማመሳሰሉን አስታውሳለው፡፡ ፅንፈኛ ዳያስፖራ በአገርና መንግስት መካከል ያለውን ልዩነት እንኳ በቅጡ አይረዳም፡፡ በአገሩ ላይ ማዕቀብ እንዲጣል ይዋትታል፡፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ አትሳፈሩ፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አትመልከቱ ይላል፡፡ እንጀራ አትብሉ ማለት ነው የሚቀራቸው፡፡ ወደአገሩ በተለያየ መልክ ለመስራት የሚመለሰውን ያገላሉ፡፡ ጉደኞች!!! አቶ ልደቱ አያሌው "መድሎት" በተባለው መፅሃፋቸው ላይ እንዳብራሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ቢመጣ ኢህአዴግን ሊያስመሰግነው ይችላል የሚል ስጋት ስለሚፈጥርባቸው አገር ቤት ገብቼ አለማለው የሚለውን ሰው ሁሉ ኢህአዴግን ለመጥቀም እንጂ አገሩን ለመጥቀም የሚሰራ ሰው ነው ብለው ለማመን አይፈልጉም፡፡ ሁለተኛው ወገን ደግሞ ስለአገሩ በጎ አመለካከት እንኳን ቢኖረውም በዕለት ተዕለት የኑሮ ወጣ ውረድ ተጠምደው ስለአገራቸው በቂ መረጃ የሌላቸው አልያም በፅንፈኛ ዳያስፖራ የታገቱ ናቸው፡፡

በቅርቡ ግን በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ይህን በጥላቻ የተሞላ ምሽግ ዋሽንግተን ላይ ሰብረውታል፡፡ ከዚህ ቀደም ሲል ካናዳ ላይ በተካሄደው የቡድን 20 ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ መንግስት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህ ከዛሬ አምስት እና አስር ዓመት በፊት የማይታሰብ በመሆኑ አዲስ ክስተት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያኑ ለኢትዮጵያ መንግስት ድጋፋቸውን የገለፁት የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ ነው፡፡ ቪቫ ዳያስፖራ፡፡ በዚህም ለአገራቸው

ያላቸውን ቀናዓኒነት አሳይተዋል። ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ በድህነት ላይ የጀመረችውን ዘመቻ ለመደገፍ እንደሚችሉ አሳይተዋል። ይህ ለውጥ የሚያበግናቸው ወገኖች ያሉ ሲሆን የኤርትራ መንግስት አንዱ ነው። እስኪገርመን ድረስ በኢትዮጵያ ላይ የሚያተኩረው የኤሬቲቪ በሰሞኑ ፕሮግራሙ አንዱ የነበረው የዋሽንግተን ሰልፈኞችን ማውገዝ ነበር። የቴሌቭዥን ጣቢያው ሠልፉ "የአሜሪካ ካዳሚ" በሚል የተዘጋጀ እንደሆነ ሲገልጽ ተስተውሏል።

ኢትዮጵያውያኑ ዋሽንግተን ውስጥ ለወዳጅም ለጠላትም ያሳዩት ሠልፍ አዲስ ምዕራፍ መሆኑ ላይ ብስማማም የፅንፈኛው ጎራ ግን ገና አልፈረሰም። መንግሥት ለሚያካሂደው የልማት ጥረት የሠጡት ድጋፍ ተገቢ መሆኑን እስማማለሁ። ይሁን እንጂ ከዓባይ ወንዝ ጉዳይ ጋር በተያያዘ መልዕክቱ የተገለጸበት መንገድ ላይ ግን ልዩነት አለኝ። መንግሥት ግብፅ በዓባይ ወንዝ ጉዳይ ላይ ያላት ያረጀና ያፈጀ አቋም መሆኑን ገልጾ ጉዳዩን በመፈክር ሳይሆን በድርድር ለመፍታት ጥረት እያደረገ ባለበት ወቅት የሠልፈኞቹ በአሁኑ ሰዓት በናይል ወንዝ ጉዳይ ላይ እንደ ሃገርና ሕዝብ መያዝ ያለብን አቋም በንድ በኩል መንግሥት ጉዳዩን የያዘበትን አቅጣጫ አጉልተን መደገፉ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ መሰል ስሜታዉነትን የተላበሱ ተጨባጭ (realistic) ያልሆኑ የአደባባይ ትዕይንቶች ለግብፅ ጫዋታ ካርድ እንዳንሰጥ መጠንቀቅ ይኖርብናል። በሰከነ አእምሮ እንጂ በስሜት የማንነዳ ሕዝቦች መሆናችንን መሆናችን ይመረጣል። ብዙ በዳያስፖራ ላይ የጻፉ ባለሙያዎች ይህ የህብረተሰብ ክፍል የማይገመት(Unpredictable) ባህሪ እንዳለው ይስማማሉ። ስለሆነም አሁን ያለውን ግለት የመጠበቅና አጠናክሮ መቀጠል አስፈላጊነት ከምንም በላይ ነው። ሰልፈኞቹ እንዳይበተኑ ኔትውርክ የመፍጠር በቀጣይም ተቋማዊ ቅርስ እንድኖረው ማድረግ ጠቃሚ ነው።ዳያስፖራው በምርጫ ወቅት ካርድ አላውና በሚኖርበት አካባቢ ያሉ የምክር ቤት አባላት በመንግስታቸው ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድሩ ሊደግፉን ይችላሉ። የተተፉ ፖለቲከኞች (rejectionist politicians) በአገራችንና የልማት አጋሮች መካከል ውዝግብ ለማራገብ በሚሞክሩበት ወቅት ደጋፊ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። በሚኖሩበት አገር፣ ከተሞች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምርና ሌሎች ተቋማት መካከል ጉድኝት ለመፍጠር ጉልህ አስተዋጸኦ አላቸው።

ህንድ በባህር ማዶ የሚኖሩ ህንዳውያንን ጉዳይ የሚከታተል ሚኒስቴር መ/ቤት አቋቁማለች። ትውልደ ህንዳውንና ህንዳውያን በዓመት አንዴ በጋራ የሚገናኙበትን

ማህበራዊ መድረክ በማመቻቸት ከአገራቸው ጋር ያላቸው ትስስር እንዲጠናከር ታደርጋለች:: ከሚሰጡት ማበረታቻዎች ውጭ በተጨማሪ የተለያዩ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ውይይቶችን በየዓመቱ ማዘጋጀትም የተለመደ ነው:: በአገራችንም በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ወቅትና የተለያዩ የፌዴራልና የክልል መንግስታት ባለስልጣናት ወደ አውሮፓና አሜሪካ በመጓዝ ውይይት ማድረጋቸውን አስታውሳለሁ:: ይህን ቀጣይ በማድረግ ዳያስፖራው በመንግስት ፖሊሲዎች ላይ ግንዛቤን ፈጥሮ እምነት እንዲኖረው ይረዳል:: አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በሚኖርባት በአሜሪካ የሚሰራጩ የራዲዮ ፕሮግራሞች ለዳያስፖራው የተሳሳተ መረጃ የሚሰጡ ናቸው:: አቶ ልደቱ መድሎት ላይ እንደገለፁት ዋሽንግተን ውስጥ የሚገኙ ራዲዮ ጣቢያዎች ስለኢትዮጵያ የሚያወሩትን ወሬ ላዳመጠ ጧት ከቤቱ በሰላም የወጣ ማታ በሰላም ወደቤቱ ይመለሳል ብሎ ለማመን ያስቸግራል ብለዋል:: ይህም የዳያስፖራውን የመረጃ እጥረት ያሳያል:: የመረጃ ክፍተቱን ለመሙላት ምን ዓይነት ፕሮግራሞች ለዳያስፖራው ያስፈልጋሉ የሚለው እንዳለ ሆኖ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ስርጭትን ዳያስፖራው እንዲያገኘው መደረጉ ጠቃሚ ነው:: ለመሆኑ በጋዜጦች አንድ አምድ ወይም የቴሌቪዝን ወጥ ፕሮግራም ቢኖረው ይበዛባቸዋል? በሌሎች አገራት ለዳያስፖራው የድረ-ገፅ መከራከሪያ ስርዓት (blogs, discussion groups dedicated portal) ማዘጋጀት የተለመደ ነው:: ጋናውያን እ.ኤ.አ. በ2020 አገራቸውን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ የማድረስ፣ ወደጠፈር መንኮራኩር የማምጠቅ ራዕይ አላቸው:: ኢትዮጵያም ተስፋ ያላት አገር ናት:: መንግስትም ራዕይ 2015ትን ሰንቋል:: በ2015 ስንዴ መለመን ታሪክ እንዲሆን ቀጠሮ ተይዟል:: ይህ ተሳክቶ አንገት ያስደፋንን ድህነት ለማስወገድ ዳያስፖራው እንደሌላው ዜጋ በአዲሱ የእድገት እና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊነት ላይ አስተዋፅዖ እንዲኖረው ለውይይት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል:: የልማት ራዕይ የፓርቲ ፖለቲካ ሳይሆን የአገር ጉዳይ ነው:: ዳያስፖራው ኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታው ናትና በፀረ-ድህነት ዘመቻው የመሳተፍ የሞራል ግዴታ አለበት:: ሰፊ አስተዋፅዖ ማበርከትም ይጠበቅበታል:: ይህ እንዲሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተለይም በውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች ከባድ ኃላፊነት አለባቸው::